

ሚያዝያ 25 | 2017 ዓ.ም

# ገንዘብ ሳይዝ በሙድ ብቻ

የደራው
መጽሔት


AD
የሚጠራህ ማን ነው?


ፀሐይ
አትጠልቅም
www.yederaw.com

# ማውጫ

ምስሉን ሲጫኑት ወደ ፈለጉት ገጽ ይወስዶታል



አፈር ሳይነካቸው በወርቅ አልጋ ይተኛሉ 9


መኪና በብድር 17


ትንሿ ሃገር ምን ይሆን እቅዷ? 12


የዶላር ነገር 21

# ማውጫ




ታላቁ ፍጥጫ 28




የደራው ሰሌዳ 37




"የባንከሯን ስልክ ብትለጥፉልን" 30



የመኪና ጨረታ 44



ገንዘብ ሳይዝ በሙድ ብቻ 39

# አውሮፓ እንሂድ

AD



FLORENCE
Walk through outstanding art, Renaissance architecture, and distinguished cultural heritage
VENICE
canals, bridges, and unique architectural style and experiance the floating city.
7
ITALY
ROME
Walk in the footsteps of emperors, gladiators, and imagine what Rome was like 2000 years ago.
እዚህ ጋር ይጫኑ
BOOK YOUR TRIP NOW!
A Spectacular Trip | 7 Days of Epic Journey!
VISA
BIG BREAKFAST
Tour VISA
Round Ticket
Transport + Tour Guide
Selected Hotel
And More
+251961609397
info@seventouroperator.com
seven
TOUR OPERATOR


www.yederaw.com





# የደራው

1ኛ ዓመት | ሚያዝያ 25 | ቁጥር ስምንት
+251919474444
www.yederaw.com
Magazine@Yederaw.com
አዲስ አበባ,ኢትዮጵያ

---

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ያፌት ገ/ህይወት(ምትኩ)

**ዋና አዘጋጅ**
ሰለሞን ከበደ
solomon@Yederaw.com

**ም/ዋና አዘጋጅ**
አቤኔዘር ወርቁ

**ሪፖርተሮች**
አሌኒ ግዛው
አያንቱ ሁንዴ

**ፎቶግራፈሮች**
ዳንኤል አበበ
ያሬድ ግስላ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
አብርሃም ቦሪስ

**ማርኬቲንግ**
ልዕልት በላይነህ
marketing@Yederaw.com
+251919474444

**ቴክኖሎጂ ዳይሬክተር**
ሱራፌል ተፈሪ

**ክሬቲቭ ዳይሬክተር**
ያፌት ገ/ህይወት

**ጸሐፊ**
ምስጢር ጌታቸው

# አፈር ሳይነካቸው
# በወርቅ አፅጋ ይተኛሉ

ለሀገርም ሆነ ለተቋማት እድገት ዋነኛ ተዋናይ በየተቋማቱ ደፋ ቀና የሚሉ ሰራተኞች ናቸው፡፡ እነዚህ የሀገር ምሰሶች በያዝነው ሳምንት ላበረከቱት አስተዋጽኦ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወስተዋል፡፡ይህ ቀን በሀገራችን ለ51ኛ ጊዜ ተከብሯል፡፡

እንደ አለም አቀፋ የላብ አደሮች ተቋም መረጃ አሁን ላይ በአለም 3.6 ቢሊየን ላብ አደሮች ይገኛሉ፡፡ የአለም የላብ አደሮች ቀን የሚከበረው በበርካታ የአለም ሀገራት የነበሩ ላብ አደሮች ለነፃነታቸው ሲሉ ያደረጉትን ታሪካዊ ትግል እና ያስመዘገቡትን ድል ለመዘከር ነው፡፡

በወቅቱ የነበሩ ላብ አደሮች በአልጠግብ ባዮች እና ክንዳቸው በፈረጠሙ ሰዎች የተጣለባቸውን ቀንበር ከላያቸው ላይ አሽቀንጥረው በመጣል ዘመን ተሻጋሪ ታሪክን ከውሀ በነጣ ላባቸው ፅፈው አልፈዋል፡፡

ዳሩ ምን ዋጋ አለው፡፡ የዚያን ዘመን ላብ አደሮች አሽቀንጥረው የጣሉት ቀንበር በዚህ ዘመን ባይመለሰም ዋጋውን ግን በከፍተኛ ሁኔታ አጥቷል፡፡ በተለይ በታዳጊ እና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ችግሩ ሰፍቶ ይታያል፡፡ለምሳሌ ያህል አፍሪካዊት የነፃነት ተምሳሌት የሆነችውን ኢትዮጵያን ማንሳት ይቻላል፡፡ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሰው ሀይል የሚገኝባት ሀገር ናት፡፡እንዲሁም ሚሊየኖች ደፋ ቀና ብለው እና ጥረው ግረው ጥቂቶች የሚበለፅጉባት ሀገርም ነች፡፡

በኢትዮጵያ ጠንክረው እየሰሩ ላባቸውን የሚያፈሱ ብዙ ናቸው፡፡ ነገር ግን የሚበለፅጉት ሌሎች ናቸው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም በዚህች ሀገር በወዞ የሚኖር ሰው የመከበር እድሉም ዝቅተኛ ነው፡፡ በዚህም አያበቃም የኢትዮጵያ ላብ አደሮች ሰቆቃ ፧ ከተገቢው በላይ ግብር በመጣል እና የአገልግሎት አሰጣቱን በማወሳሰብ ለፍቶ አዳሪዎችን መዋቅራዋ በሆነ መንገድ መበደልም ይስተዋላል፡፡

በከምንም በላይ ችግሩን አስከፊ የሚያደርገው መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለሚበለፅጉ ተኝቶ በይዎች የሚሰጣቸው ከፍተኛ ክብር እና ቦታ ነው፡፡

ታድያ ማህበረሰቡ ለነዚህ በጨረቃ ለሚበለፅጉ ባለፀጋዎች የሚሰጡትን የተሳሳተ ግምት ወደ ጎን ትቶ በነጭ ላባቸው ሀገር እያቀኑ ላሉ ላብ አደሮች ተገቢውን ክብር እና ቦታ መስጠን ግድ ይላል፡፡

መንግስትም ለፍቶ አዳሪዎችን በማገዝ ለሀገር የሚያበረክቱትን ሚና እንዲያጎሉ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡
የሀገራችንን ራዕይ ለማሳካት በርትታቹ እየሰራቹ፣እየተጋቹ፣ጊዜያቹን እየሰዋቹ ፣ እድሜያአችሁን እና ጉልበታቹሁን እየሰጣቹ ፣ ነገን ዛሬ ላይ እየሰራችሁ የምትገኙ፣ በንፁህ ላባቹ ሀገር ለምትገነቡ የኢትዮጵያ ሰራተኞች (ላብአደሮች) እንኳን አደረሳችሁ፡፡

የፈሰሰው ላባቹ ዋጋ የሚያገኝበት ዘመን እንዲሆንላቹ ተመኘን!!!

ለስራ ከተነሳን "ፀ ሐ ይ  አ ት ጠ ል ቅ ም ! "

የደራው ዝግጅት ክፍል
የሚሰሩ እጆች ሁሉ ጥበበኞች እንደሆኑ ያምናል!

የአዘጋጆቹ መልዕክት!

የደራው
መጽሔት
ፀሐይ አትጠልቅም!


AD
ህልሞት ሊሳካ ነው!
UTOPIA
Making Dreams Come True
የቤንዚል ወጪ 0 ብር ሆነ ! የኤሌክትሪክ መኪና ኢቮሊሽን ይቀላቀሉ !
ዩቶፕያ ቴክኖሎጂ
+251 975 80 80 80
+251 976 80 80 80
8022
ugmfund.com
የኤሌክትሪክ መኪና በመንዳቶ ! በ15 አመት ለነዳጅና እና ለዘይት የሚያወጡትንከ 2 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ያትርፉ !

# ትንሿ ሀገር ምን ይሆን እቅዷ?

**“ የጅቡቲ ኢትዮጵያውያንን የማስወጣት ዕቅድ ምክንያቱ ፖለቲካዊ ነው፡፡ ሀገሪቱ በእቅዷ መሰረት በሺዎች የሚቆጠሩትን ስደተኞች ጨክና ታባርር እንደሆነ የምናየው ይሆናል፡፡ በእቅዷ ገፋታ ከሄደችበት በእሷም ላይ የሚያስከትለው መዘዝ አለ “ – አበባው ምናዬ (ዶ/ር)**

የጅቡቲ መንግስት በሀገሩ የሚገኙ የውጭ ሀገር ዜጎች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በፈቃዳቸው ለቀው እንዲወጡ፣ ካልሆነ ግን በግዳጅ እንደሚባረሩ አስታውቋል፡፡

ሰነድ አልባ የሆኑ የውጭ ሀገር ዜጎች ሀገሪቱን ለቀው እንዲወጡ የተሰጣቸው ቀነገደብም፣ በመጪው ቅዳሜ ይጠናቀቃል፡፡

ይህ መንግስታዊ ትዕዛዝ ያተኮረው በእኛ ላይ ነው የሚሉት በዚያች ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በበኩላቸው፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ መውጣት ስለማንችል ተጠንቀናል ብለዋል፡፡ ከዚያ አልፈው የመንግስትን እርዳታ ጠይቀዋል፡፡

ቲክቫህ ኢትዮጵያ በጉዳዩ ዙርያ ሙያዊ አስተያየት እንዲያጋሩ የጠየቅናቸው ባለሙያ በበኩላቸው፣ ይህ የጅቡቲ እቅድ ፖለቲካዊ ይዘት እንዳለው ገልፀው፣ ወደ ተግባር ከተሸጋገረ ለእሷም ከባድ መዘዝ ያስከትላል ይላሉ፡፡



በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የማህብረሰብ ሳይኮሎጂ መምህር እና የፍልሰትና የስደት ጥናት ማዕከል አስተባባሪ የሆኑት አበባው ምናዬ (ዶ/ር)፣ ጉዳዩ ጂኦፖለቲካዊ ነው፣ መፈታትም ያለበት በውይይት ነው ብለዋል፡፡

አበባው ምናዬ (ዶ/ር) ምን አሉ ?

“ ብዙ ጊዜ እንደምናየው እንዲህ ዓይነት ውሳኔ የሀገራት ፖለቲካዊ ግንኙነት ነፀብራቅ ነው፡፡ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች በሰዎች ፍልሰት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አላቸው፡፡

መልካም ግንኙት ሲኖርህ የሌላ ሀገር ዜጎችን ትንከባከባለህ፣ አሉታዊ ግንኙነት ሲኖርህ ደግሞ የሌላውን ሀገር ዜጋ ታስወጣለህ፡፡ የጅቡቲም አንዱ ምክንያት ይኼ ሊሆን ይችላል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ፣ በሱዳን በኩል ያለው የፍልሰትና የስደት በር አሁንም እንዳለ ቢሆንም ብዙ ችግር ገጥሞታል፡፡ ስለሆነም፣ ከኢትዮጵያ የሚነሱ ፍልሰተኞች ወደ ጅቡቲ መስመር አቀጣጫ ቀይረዋል፡፡ ይህ መስመር በጣም ተጨናንቋል አሁን ከሌሎቹ በበለጠ፡፡ ይህም በፍልሰተኞች ፍሰት ጅቡቲን ሊያስመርራት ይችላል፡ ፡ ነገር ግን፣ አሁን ጅቡቲ ውጡልኝ እያለቻቸው ያለችው ነባር ፍልሰተኞችን ነው፡፡ አዳዲሶቹን አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ ነገሩን ፖለቲካዊ ያደርገዋል፡፡ “

ፖለቲካዊ ምክንያቱ ምንድነው ?

“ የኢትዮጵያ የወደብ አማራጮችን መፈለግና በጅቡቲ ወደቦች ላይ ጥገኛ ላለመሆን የሚደረገው ጥረት ያስደነግጣታል፡፡ ኢትዮጵያ ደግሞ አማራጮችን እያፈላለገች ነው ያለችው፡፡

ከኢትዮጵያ በጣም ከፍተኛ ገቢ ሲያገኝ የነበረ ሀገር፣ ኢትዮጵያ የሌሎች ሀገራት ወደቦችን ለመጠቀም ስታማትር ይደነግጣል፡፡

ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር ሰላም የፈጠረች ጊዜ ለጅቡቲ አስደንጋጭ ነበር፡፡ ‘ ኢትዮጵያውያኑ ኤርትራ ላይ ወደብ ካገኙ፣ ጥለውኝ ይሔዳሉ ‘ ነው የምትለው፡፡

ስለዚህ ስደተኞችን የማባረር እቅዱ ትርጉም፣ ‘ሌላ ወደብ አታማትር፣ እዚሁ ቆይልኝ፣ ካማተርክ ግን እኔ ደግሞ ያለችኝን ዱላ እወረውራለሁ ነው። ‘ ይህን ዱላ ትወረውረዋለች ወይ የሚለውን፣ የምናየው ይሆናል። ከተወረወረ ግን ለሁለቱም ሀገራት ጎጂ ነው የሚሆነው።

በርግጥ የተወሰኑ በየመንገዱ የምታገኛቸውን ሚስኪኖች ከመንገድ ለቃቅማ ልታስወጣ ትችላለች። የኢትዮጵያን ግብረመልስ ለመመዘንና ለማየት የሚደረግ ማስፈራሪያ ነው የሚመስለኝ። ሆኖም፣ ከኢትዮጵያ በኩል ይፋዊ የሆነ ግብረ መልስ አልተሰማም እስካሁን።

ጅቡቲ ወደ ተግባር ከተሸጋገረች፣ ከዚህ በኩል የሚገጥማት ግብረመልስ ምን ሊሆን እንደሚችል አናውቀውም። “

ጅቡቲ ወደ እርምጃ ብትገባ ጉዳቱ ምንድነው ?

“ ይህ እቅድ፣ ከማስፈራራት አልፎ ቀጥታ ወደ እርምጃ የሚለወጥ ከሆነ፣ ያልተጠበቀ ጉዳት ነው የሚያስከትለው። ጅቡቲም ትልቅ ችግር ውስጥ ትወድቃለች። አንደኛ፣ ያች ሀገር ሰራተኛ የላትም። በብዛት የሚሰሩት የእኛ ሰዎች ናቸው። ስለዚህ ይጎዳታል። ሁለተኛ ደግሞ ኢትዮጵያ አፀፋዊ እርምጃ ብትወስድስ የሚለው መምጣት አለበት።

ውሀ እና መብራት ከዚህ ነው የሚቀርብላት፣ ጫትም ጭምር። ሀገሪቱ በኢትዮጵያ የወደብ ኪራይ ገቢ ላይ በእጅጉ ጥገኛ ናት። የጅቡቲ ዜጎች ድሬዳዋ ድረስ እንደፈለጉ ነው የሚኖሩት። እነዚህ ጥቅሞች እያገኘች፣ የኢትዮጵያን ዜጎች ላስወጣ ማለቷ፣ ለማስፈራራት ነው እንጂ የሚመስለኝ፣ የሚተገበር መሆኑን እጠራጠራለሁ።

እነዚህን ጥቅሞች ወደ ጎን አድርጋ ለምን እንደዛ እንዳሰበች ሊገባኝ አልቻለም በእውነት። የሚታሰብ ነገር አይደለም። እቅድዋን ብትተገብረው፣ እኛም እንጎዳለን፣ ግን ጅቡቲ ላይ የሚያስከትለው መዘዝ የበለጠ ነው የሚሆነው። “

ባለሙያው በሰጡት ምክረሀሳብ ምን አሉ ?

“ በጅቡቲ ከ250 እስከ 300 ሺህ ኢትዮጵያዊ እንደሚኖር ነው የሚገመተው፡፡ ይህ ማለት ከጅቡቲ ህዝብ አንድ አምስተኛው ያህል እንደ ማለት ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ አብዛኛውን የማጓጓዝ አቅም ከዬት ታመጣለች፡፡

ስደተኛ ከመደንገጥ ይልቅ፣ ይህን ሁሉ ሰው እንዴት በተደራጀ መልኩ ከሀገር ሊያስወጡት እንደሚችሉ ማየት ነው የሚሻለው፡፡ በጅቡቲ አቅም ስደተኛውን እንዴት አድርገው ነው አደራጅተው ወደ ሀገሩ ሊመልሱት የሚችሉት፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ይህ እቅድ ጉዳት ስለሚያስከትል ከጅቡቲ መንግስት ጋር መወያየት ነው ያለበት፡፡

ይሔ ፖለቲካዊ ሪአክሽን ነው፣ ጂኦፖለቲካዊ ነው፣ መፍትሔው ውይይት ነው፡፡

ከኢትዮጵያ በኩል ግፊት ቢደረግ፣ ጅቡቲ እቅዷን ዳግም የምታጤነው ይመስለኛል፡፡ ቁጭ ብሎ መወያየት የስፈልጋል፡፡

ለሁሉም ግን መዘጋጀት ጥሩ ነው፡፡ ስደተኛው ደግሞ መንግስት የሚሰጠውን አቅጣጫ ተከትሎ ሰነዶቹን እያዘጋጀ፣ የሚሆኑትን ነገሮች መጠባበቅ አለበት፡፡ የጅቡቲ መንግስት ጨክኖ ይህን እርምጃ የሚወስድ ከሆነ፣ ኢትዮጵያ ብዛት ያለውን ተመላሽ ስደተኛ ለመቀበል መዘጋጀት አለባት፡፡ “





የድል
ዋዜማ
ትጋት ነው!




## ኢትዮፒካር መኪና አስመጪ ከአሚጎስ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ህብረት ስራ ማህበር ጋር በመተባበር በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መኪኖችን ለተጠቃሚዎች አስረከበ።

በዛሬው ዕለት፣ ሚያዚያ 25 ቀን 2017 ዓ.ም.፣ ኢትዮፒካር መኪና አስመጪ ከአሚጎስ ቁጠባና ብድር ተቋም ጋር በነበራቸው ስምምነት መሰረት ለ15 የሚሆኑ ቁጠባቸውን በአግባቡ ያጠናቀቁ የኢትዮፒካር ደንበኞች የኤሌክትሪክ መኪናዎቻቸውን ተረክበዋል።

አሚጎስ ቁጠባና ብድር ተቋም ከኢትዮፒካር ጋር ከተፈራረሙበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ ቅድመ ቁጠባቸውን ላጠናቀቁ 100 ደንበኞች የኤሌክትሪክ መኪናዎችን አስረክቧል። በቀጣይም እስከ ሰኔ 30 ድረስ ለተጨማሪ 50 ደንበኞች መኪኖችን ለማስረከብ እቅድ ይዞ እየሰራ መሆኑን ገልጿል።

ኢትዮፒካር መኪና አስመጪ በቀጥታ ግዢ እንዲሁም በባንክ ብድር አማራጭ የሚገኙ የኤሌክትሪክ መኪኖች የፋብሪካ ዋስትና ያላቸው ሲሆን እስካሁንም ከ1000 በላይ ለሚሆኑ ደንበኞች ከባንክ እና ከቁጠባና ብድር ተቋማት ጋር በመተባበር መኪኖችን አስረክቧል።


Walia Tender
ዋልያ ቴንደር
ከመላው ኢትዮጵያ የሚወጡ ሁለንም አይነት የጨረታ ማስታወቂያዎች በቀላሉ!
ከ 7 አመት በላይ ያለምንም ማቆራረጥ በታማኝነት፣
ጨረታዎች በወጡበት ፍጥነት፣
ተመጣጣኝ ዋጋ ና ለአጠቃቀም ምቹ፣
በቴሌግራም ፣ በአፕ ና በድረገጽ አማራጮች፣
አሁኑኑ ይመዝገቡ!
+251942125616
+251919415260
Walia Tender
www.waliatender.com


Temer
PROPERTIES
ለበዓል የወጣ
ታላቅ ቅናሽ!
90 ካሬ በ5,778,000 ብር
130 ካሬ በ8,346,000 ብር
ቴምር ሪል እስቴት
ሳር ቤት ላይ
0912685310


AD
የደራው
ገበያ
በቅርብ ቀን



# ኢትዮጵያ አባል በሆነችው ብሪክስ የንግድ ልውውጥ ከዶላር እየራቀ

የሩሲያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌ ላቭሮቭ እንዳስታወቁት ኢትዮጵያን ጨምሮ አባል የሆኑት የብሪክስ አገራት (ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ህንድ፣ ቻይና፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ግብፅ፣ ኢንዶኔዢያ፣ ኢራን እና የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች) በንግድ ልውውጣቸው ከአሜሪካ ዶላር እየራቁ ሲሆን ከ65 በመቶ በላይ የሚሆነው ንግድ አሁን በአባል አገራቱ ብሔራዊ ገንዘቦች እየተከናወነ ነው።

ሚኒስትሩ ይህንን ያሉት በብራዚል በተካሄደው የብሪክስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ማጠቃለያ ላይ በሰጡት መግለጫ ሲሆን፣ ይህ አዝማሚያ ቡድኑ በፋይናንስ ረገድ ያለውን ነፃነት ለማጠናከር ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል ብለዋል።


ላቭሮቭ አክለውም “BRICS Pay” የተባለ ገለልተኛ የክፍያ ስርዓት ለመመስረት የሚደረጉ ውይይቶች እየተሻሻሉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በተጨማሪም የBRICS የገንዘብ ሚኒስትሮች እና የማዕከላዊ ባንክ ገዥዎች በካዛን ጉባኤ በተሰጠው መመሪያ መሠረት በጋራ ንግድ ውስጥ ብሔራዊ ገንዘቦችን በንቃት ለመጠቀም ተስማምተዋል።

ይህ እርምጃ ብሪክስ በምዕራባውያን የገንዘብ ስርዓቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ የፋይናንስ መሠረተ ልማት ለመገንባት የሚያደርገውን የጋራ ጥረት ያሳያል።

በቅርቡ ኢትዮጵያ ለአዲሱ የልማት ባንክ (ቀደም ሲል የብሪክስ ልማት ባንክ በመባል ይታወቅ የነበረው) በይፋ አባልነት ለመቀላቀል ማመልከቻ ማስገባቷና የዚህ ሂደት በቅርቡ እንደሚጠናቀቅ ገልፃ እንደነበር ይታወሳል።
#cnp


"ተስፋችንን እንይ"




## የታክሲ እና የቤንዚል ሰልፍ ሰልችቶታል?

UTOPIA
Making Dreams Come True

እንግዲያውስ ድርጅታችን ዩቶፕያ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን “ዩቶፕያ ግሪን ፈንድ በመተግበር በ5 አመት 10,000 አባላትን የመኪና ባለቤት ያደርጋል!

እንዴት?

1. በየመኪና ሊዝ ከቅድመ ክፍያ ጋር ፓኬጅ

ቅድሚያ ከ30% ማለትም 897,000 ብር ጀምሮ በመክፈል መኪናውን በ 3ወር ጊዜ ይረከባሉ !

ወይም

2. በየመኪና ሊዝ ከእቁብ ጋር ፓኬጅ

በቀን ከ292 ብር ጀምሮ በመቆጠብ በየ4ወሩ ከ100 እስከ 600 ደንበኞች በሚወጣ የመኪና እጣ ከ3 ወር እስከ 3 አመት በሚሆን ጊዜ የመኪና ባለቤት የሚሆኑበትን እድል እመቻችተናል፡፡

- የረጅም ጊዜ ዋስትና ፣ ፈጣን የቻርጂንግ ሰርቪስ፣ የተሟላ ጥገና እና መለዋወጫ አመቻችቷል፡፡

- የመመዝገቢያ ክፍያ በግል 89,700ብር ወይም በጋራ ለ3 በመሆን 29,900 ብር

**ዩቶፕያ ግሪን ሞቢሊቲን ይቀላቀሉ !**
**በ www.ugmfund.com ፈጥነው ይመዝገቡ !**
**ይጫኑት ወደ ድረ-ገጹ ይወስደታል**

**አድራሻ :-**
**ቅ/ር 1. ከአምባሳደር ሲኒማ ፊትለፊት ከመከላከያ መስርያ ቤት አጠገብ በሚገኘው ፐፐሲኖስ ህንፃ ምድር ላይ !**
**ቅ/ር 2. ቦሌ መድሀኒያለም ሞል 7ኛ ፎቅ**

**ኮል ሴንተር : - 8022**

**ሞባይል :- 09 75 80 80 80 / 09 76 80 80 80 /**
**09 45 84 44 44 / 09 45 94 44 44**

AD



የደራው ላይ
ያስተዋውቁ
ገበያዎን ያድሩ!

ያግኙን : 0919474444




## ድምፃውያን እና ጋዜጠኞች ለፍፃሜ ደርሰዋል

ጋዜጠኞች ቲክቶከሮችን በማሸነፍ ለእሁዱ የፍፃሜ ጨዋታ የደረሱ ሲሆን ድምፃውን የአርቲስቶች ቡድንን በማሸነፍ የዋንጫው የመጨረሻ ተፋላሚ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

ሁለቱም ጨዋታዎች ከፍተኛ ፉክክር የታየባቸው ሲሆኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችም በሜዳ ተገኝተው ውድድሩን ተመልክተዋል፡፡
የፍፃሜው የዋንጫ ጨዋታ እሁድ 9:00 ሰዓት በቢሪሞ ሜዳ ይደረጋል፡፡
የፍፃሜ ጨዋታውን ለመመልከት አሁኑኑ ትኬቶን ከቴሌ ብር ላይ ይግዙ ሽያጩ ለመቄዶንያ ገቢ የሚውል ነው፡፡
Celebrity sports festival powered by Pepsi
የታዋቂ ሰዎች ስፖርታዊ ዉድድር ከፔፕሲ ጋር



Every child deserves a chance to learn, to grow, and to thrive.

# Creating an impact **since 1998.**

"Empowering the future, one child at a time, through the transformative gift of education and the strength of women in Ethiopia since 1998 – because investing in today's youth and uplifting women creates a brighter, more equitable tomorrow."

FANOS

Integrated Community Development Organisation

Reg: 1084098 - Established January 1998

fanos.org.uk




## “የባንከሯን ስልክ ለጥፋልን!” የባንክ ደንበኛ

ከገንዘብ ጋር ያን ያህል የቀረበ ግንኙነት የለንም፡፡ ሀብታሞች ሚሊየነር እንደሚባሉት እኔ ችስታ ስለሆነኩ ችስቲየነር ነኝ፡፡ ሀብታም የመሆን ፍላጎትም ቢሆን ያን ያህል የለኝም፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስም የምወደው ጥቅስ መጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 30፡7 ላይ ያለው “ሁለት ነገር ከአንተ እሻለሁ፥ ሳልሞትም አትከልክለኝ፤ ከንቱነትና ሐሰተኝነትን ከእኔ አርቃቸው፤ ድኅነትንና ባለጠግነትን አትስጠኝ፤ ነገር ግን የሚያስፈልገኝን እንጀራ ስጠኝ፥ እንዳልጠግብ እንዳልክድህም፡፡ እግዚአብሔርስ ማን ነው? እንዳልል፤ ድሀም እንዳልሆን እንዳልሰርቅም፥ በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል፡፡” የሚል ነው፡፡

ብር ባይኖረኝም በርከት ያሉ የባንክ ደብተሮች ግን አሉኝ፡፡ መንገድ ላይ ስሄድ በተለይም በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ዎክ ላድርግ ብዬ ከወጣሁ ከረባት፣ ሸሚዝ፣ የጨርቅ ሱሪ እና ቆዳ ጫማ ለብሰው በእጃቸው በርከት ያለ ወረቀት ይዘው በትህትና ሲያናግሩኝ ይሉኝታ እና ሼም እየያዘኝ 25 ብር እየሰጠሁ ቡክ እቀበላለሁ፡፡ ሴቶች ሲሆኑ ደግሞ የሚያስከፍቱት ለምን የአፍጋኒስታን ባንክ አይሆንም ትዳር ስላልያዝኩኝነው መሰል የባንኩን ስም ሳላይ ሁላ ነው የምከፍተው፡፡ መቼም ዘንድሮ የባንክ ቡክ እና አፍ መክፈት ቀላል ሆኗል፡፡

የኢኮኖሚ እና የፋይናንስ ባለሙያ ባልሆንም የሀገራችን ባንኮች ኢኮኖሚውን ከማሳደግ እና የሰፌውን ህብረተሰብ ኢኮኖሚ ከመደገፍ ባሻገር ደንበኞችን በመቀራመት ላይ ትኩረት አድርገው እየሰሩ ነው፡፡ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚመሰረቱ ባንኮች በየወገናቸው የወረደ ሀሳብ እያንጸባረቁ ደንበኞችን በዘር እና በብሔር አለፍ ሲልም በሃይማኖት እያማለሉ ወደ ራሳቸው ለመውሰድ ሲዳክሩ ይታያል፡፡ እርግጥ ነው ካሉት ውስን ባንኮች ብሔራዊ የሆኑ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያገለግሉ እና ተጽእኖ የማይታዩባቸው አሉ፡፡

የባንኮቻችን ሌላኛው ችግር ሰራተኛ ቅጥር ላይ ነው፡፡ ዳጎስ ያለ ደመወዝ እንደመክፈላቸው እና በርካታ የሰው ሀይል በሀገር አቀፍ ደረጃ እንደመቅጠራቸው ሙስና የሚጠበቅ ቢሆንም በነፍስ ወከፍ ለአንድ ሰው ቅጥር አንድ መቶ ሺህ ብር ከዚያ በላይ እንደ ደመወዙና ደረጃው ከዚያ በላይ ብር እንደሚጠየቅ እንሰማለን፡፡ ያንንም ለመቅረፍ አንዳንድ ባንኮች አዳዲስ የፈተናና የቅጥር ስረርአት መዘርጋት መጀመራቸው የሚበረታታ ቢሆንም ሙስናውን መኖሩን ያሳብቃል፡፡

ችስቲየነር እንደመሆኔ ባንክ ውስጥ ብዙ ብር አላስቀምጥም፡፡ ላስቀምጥ ብልም የሆነ የኑሮ ቀዳዳ ስለሚኖርብኝ ያችን ለመድፈን ስል ወዲያው አወጣታለሁ፡፡ በነገራችን ላይ ማንኛውም አይነት ብር ለማውጣት አልሳቀቅም፡፡

ያ እንዲሆን ደግሞ ያደረገው የዩኒቨርስቲ ጓደኛዬ የነበረው ይታገስ ነው፡፡ ይቴ ቡኩ ውስጥ የነበረችውን አምስት ብር በድፍረት ሄዶ ለማውጣት ሞክሯል፣ ለእኔ አርአያ ሆኖኛል፡፡ እኔም በተደጋጋሚ 20 30 እና 40 ብሮችን ምንም ሳይመስለኝ ባንክ ሄጄ ስጡኝ ብያለሁ፡፡

የባንኮቻችን ሌላኛው ጥቅም ለመንገድ ተጓዦች ነው፡፡ ወደ ሆነ ቦታ እየሄድኩ ሰው ደውሎ የት ደረስክ ቢለኝ መጀመሪያ የማደርገው ነገር ባንክ ቤቶችን ፈልጌ የቅርጫፋን ስም አይቼ እዚህ ደርሻለሁ ማለት ነው፡፡ አሁን ላይ ከገጠር እስከ ከተማ ባንኮች የሌሉበት ቦታ ስለሌለ ሁሉንም አካባቢዎች ከእነ ጥንታዊ ስያሜዎቻቸው በቀላሉ ማወቅ ይቻላል፡፡ አካባቢዎቹ የሚታወቁባቸውን ነገሮችንና ታዋቂ ግለሰቦች ስም ቅርንጫፎችን በመሰየም አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ እናት ባንክ ለሀገራችን ትልቅ ውለታ በዋሉ እና አውንታዊ አስተዋጽኦ ባበረከቱ እንስቶች ስም ቅርጫፎችን በመሰየም ስማቸው እንዲነሳ እና ታሪካቸው እንዲዘከር እያደረገ ይገኛል፡፡
ባንኮቻችን ሌላኛው ፋክክራቸው ሎጎ ላይ ነው፡፡ በየጊዜው ሎጎ በመቀየር ይታወቃሉ፡፡ ይቀይራሉ የሚለው ቃል ራሱ አይገልጻቸውም፡፡ አንድ እና ወጥ የሆነ የራሳቸው ብራንድ ይዞ መቀጠል ያቃታቸው ይመስለኛል፡፡ በየሰአቱ ሎጎ እና መሪ ቃል እየቀየሩ ተወዛግበው ያወዛግቡናል፡፡

አንድ ቀን እግር ጥሎኝ ወደ አንድ ባንክ ጎራ አልኩኝ፡፡ በአጋጣሚ ወደ አንድ ተፈጥሯዊ መስህብ ለመጎብኘት ጉዞ ላይ ነበርን፡፡ መኪናው ውስጥ የነበርነው ሰዎች ምሳ ለመብላት ወረድን፡፡ እኔም ኪሴ ውስጥ በቂ ብር ስላልነበረኝ ያለችኝን ለማውጣት ወደ አንድ ባንክ ቅርንጫፍ ጎራ አልኩኝ፡፡ ከተማው ትልቅ ከተማ ነው በዛ ላይ የከተማው የገበያ ቀን ነውና የባንኩ ቅርንጫፍ በሰው ተጥለቅልቋል፡፡ የምሳ ሰአት በመሆኑ ደግሞ በደንበኛ ማስተናገጃ መስኮቶቹ በኩል ያሉት ሦስት ሰራተኞች ብቻ ነበሩ፡፡

የማወጣውን የገንዘብ መጠን የወጪ ማዘዣ ወረቀቱ ላይ ጽፌ ከተከመረው የባንክ ደብተር ስር አስቀመጥኩኝ፡፡ የማይደርሰኝ አይነት ስሜት ተሰምቶኛል ነገር ግን በቂ ብር ባለመያዜ የግድ መጠበቅ አለብኝ፡፡ ከጎኔ ገበያተኞች፣ ነጋዴዎች፣ ባለሀብቶች፣ የቢሮ ሰራተኞችና በብዙ የስራ መስኮች ላይ የተሰማሩ ሰዎች ወረፋቸውን ይጠብቃሉ፡፡ ሁሉም በሚባል ደረጃ ትዕግስታቸው ተሟጦ፤ ምሬታቸውን ይገልጣሉ፡፡
እነሱ ብቻ አይደሉም፡፡ እኔ ራሴ ባንክ ገብቼ በአገልግሎታቸው ረክቼ የምወጣው ከስንት አንድ ነው፡፡ እኔ ስገባ ጠብቆ ነው መሰለኝ ሆን ብሎ ወረፋ ይበዛል፣ መብራት ይጠፋል፣ ሲስተም ይጠፋልና ምርር አድርገውኝ ነው የምወጣው፡፡ በተለይ ይኼ ሲስተም የሚባለው ነገር ሲጠፋ ታግቶ ብር የተጠየቀበት ይመስል አስለቅሶን ነው የሚመጣው፡፡

የደንበኞችን መማረር እየሰማሁ የባንኩን ቅርንጫፍ ዙሪያ ገባ ስቃኝ አንድ ጥግ ላይ የደንበኞች አስተያየት መስጫ አጀንዳ አየሁኝ፡፡ ወረፋው እስኪደርሰኝ ለምን ገለጥለጥ አድርጌ አላነበውም ብዬ አሰብኩ፡፡ አጀንዳውን ስገልጠው ብዙ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡ እውነት ለመናገር ያን ያህል በርካታ አስተያየቶች ይኖራሉ ብዬ አልጠበቅኩም ነበር፡፡ አስተያየቶችን ቀስ በቀስ ማንበብ ጀመርኩ ከአስተያየቶቹ የወደድኳቸውን እንዲህ አቀረብኳቸው፡፡

1ኛ አፍቃሪው ፦ ጥግ ላይ የምትቀመጠው ቆንጆዬ ልጅ ስልኳን እና አድራሻዋን ብትለጥፋልን! ለሌላ አይደለም ለደንበኛ እርካታ ሲባል ፡፡

2ኛ አማራሪ ፦ ኧረ ውይ አሁንስ አበዛችሁት! ቢያንስ ሲስተማችሁን አስተካክሉ፡፡ ሁሌ ሲስተም የለም፡፡ እውነት ይደብራል፡፡ በዛ ላይ ወረፋው! ምናለበት አሁን ሰው ሲበዛ ቀሪዎቹን መስኮቶች ክፍት ብታደርጓቸው፡፡ ኤቲ ኤማችሁስ ቢሆን ራሱ ካርድ ይውጣል፡፡ መዋጥ ብቻ አይደለም ውጦ ያስቀራል፡፡ ሳይከፍል ብር ይቆርጣል፡፡ ኧረ አታስመርሩን እባካችሁ! እኛ ገንዘባችንን አምነን ሰጥተናችሁ እናንተ እስክርቢቶ አስራችሁ ታስቀምጣላችሁ፡፡

ደግሞ በገዛ ገንዘባችን ከዚህ በላይ አታወጡም ሞናሞን የምትሉትን ነገር አቁሙ፡፡ ለማንኛውም እኔ መሮኛል አስተካክሉ ብያለሁ አስተካክሉ፡፡

3ኛ ተቃዋሚ ፦ ጎበዝ አሁን አሁን ኢኮኖሚያችን እየቆረቆዘ ነው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነታችን እየቀነሰ ነው፡፡ የአለም ባንክ ብድር ለማበደር እንኳን አይፈልግም፡፡ እስኪ አሁን ሁለት መቶ ብር ምን ይገዛል? ምንም! እስኪ ራሳችንን እንጠይቅ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመነምን ነው፡፡ እና ምን ለማለት ፈልጌ ነው ሌሎች እኛንም አትርሱን ፡፡

4ኛ ካድሬ ፦ ክቡር የባንኩ ማናጀር፤ ክቡራን የቅርንጫፉ የማኔጅመንት አካላት፤ ክቡራን የባንኩ ሰራተኞች፤ ክቡራትና ክቡራን፡፡ ከሁሉ አስቀድሜ ባንካችሁ እና ባንካችን ባለፉት አመታት እና በበጀት አመቱ ላስመዘገበው እድገት እና ስኬት እንኳን ደስ አላችሁ እያልኩ ለዚህ ስኬት በተለይም የእኛ የደንበኞች የእናንተ የሰራተኞች እንዲሁም የባንኩ አመራሮች ሚና በጉልህ የሚነሳ ነው፡፡ በተለይም በሀገራችን እና በአለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝና ጦርነት ምክንያት የተፈጠረውን የኢኮኖሚ መንገጫገጭ በሰራተኞች ትጋትና በድንቅ የአመራር ብቃት በማለፍ አመርቂ ውጤት አስመዝግባችኋል፡፡ ባንኩ ኪራይ ሰብሳቢነትን በመታገል ረገድ ከሌሎች ተቋማት የተሻለ አፈጻጸም አሳይቷል፡፡ በተረፈ ባንኩ የሚታዩበትን ችግሮች ከስሩ ለመቅረፍ በስብሰባዎች፣ በባንካችሁ ኮንፍረንሶችና ጉባኤዎች በጥልቅ ተሀድሶ መንፈስ በመገምገም ህብረ ብሔራዊ የሆነውን የደንበኞች አስተያየት በመቀበል ለለውጥ መትጋት ይሻል፡፡ ባለፈው ስርአት ባንካችን የግለሰቦችን ረጃጅም እጆች ተቋቁሞ እዚህ መድረሱ ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ልክ እንደ ለውጡ መንግሥታችን ባንኩ የውስጥ እና የውጭ ጠላቶችን ተቋቁሞ የእድገት እና የትራንስፎርሜሽን እቅዱን ለማሳካት መንግስት የሚያደርገውን ርብርብ እንዲያግዝ አሳስባለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

5ኛ ENGLISH ፦ hi all. I would like to give my comments. I hope you will take it. Your internet  system is very late like tortoise. There is a problem with your accountants too They aren’t skilled enough. I appreciate your internet banking and mobile banking so keep up the good work always be on the latest version. Kin-dely


6ኛ አነቃቂ ፦ ወዳጆቼ እንዴት ናችሁ? ይህችን ጽሑፍ ለትንሽ ሰከንድ በማንበብ ራሳችሁን አንቁ። ስንቶቻችሁ ናችሁ በራሳችሁ ውስጥ ሀገር እና ወገን መለወጥ የሚችል እምቅ አቅም እንዳላችሁ የሚታውቁት? እስኪ ራሳችሁን ጠይቁ? ከጠየቃችሁ፤ መልሱ አዎ ነው! አይደለም ሀገርን አለምን መለወጥ የሚያስችል ትልቅ አቅም በውስጣችሁ ተከማችቷል። ብቸኛ የሚጎላችሁ ነገር አምናችሁ መቀበል ነው። ችሎታችሁ ከእናንተ እንዲወጣ ሌላው ሰው እንዲያየው በር ክፈቱለት። አሁን ባንክ ውስጥ ነው አይደል ያላችሁት? ሲቆጠር የምታዩት ብር የእናንተ ይሆናል እመኑ። አካውንታንት ሆንክ ብር ልታንቀሳቅስ የመጣህ ሰው! አንተ ትችላለህ! አይደለም ይህን ብር ባንኩን የራስህ ማድረግ ትችላለህ። ከአንተ የሚጠበቀው ራስህን ማድመጥ፣ ማክበር ለራስህ ቦታ መስጠት፣ ከዛ ውስጥህ ለሚንተገተገው አቅምህ በር መክፈት፤ ውጤቱ ስኬት እና ክብረት ይሆናል። እኔም አሁን እንደእናንተ ነኝ ከሰማኸኝ ነገ በስኬት ማማ አብረን እንሳፈፋለን ወዳጄ።

እነዚህን እና ሌሎች እጅግ በርካታ አስተያየቶች አንብቤ ቀና ስል አሁንም ወረፋው አልደረሰኝም። እኔስ አስተያየት ከሰጡት የየትኛው ወገን ነኝ አልኩ። ከአማራሪዎቹ

በናትናኤል ዮርዳኖስ ለ’የደራው መጽሔት


WHERE QUALITY MEETS PASSION
Prestige Addis
WWW.PRESTIGEADDIS.COM
BEYOND THE SCREEN
with
LEUL
SISAY
06
MAY
SATCHMO CENTER, US EMBASSY 🇺🇸
8:00 ETHIOPIAN TIME
Prestige Addis
IN PARTNERSHIP WITH
AMERICAN SPACES ETHIOPIA

# የጀርባው ሰሌዳ



Part of Creative African CSR initiative
Marketing School (The Perfect Manager)
HOW TO RUN BUSINESS IN ETHIOPIA?
Free Virtual Training
3 Days (May 07 - 09)
+251922298823
Round 02 - ሁለተኛ ዙር
ምሽት ከ1:00-2:30 ሰዓት
CERTIFICATE OF PARTICIPATION UPON COMPLETION WITH 2 DAYS OF MENTORSHIP SESSIONS (250 ETB - ብር)
Marketing School




POWERED BY | GDG ON CAMPUS AASTU
AASTU
TECH FEST
LEARN, BUILD, COLLABORATE, CONNECT
NEW GRADUATION hall
7th MAY
FULL DAY
WEDNESDAY
EARLY BIRD REGISTRATION NOW OPEN!
EVENT IN ADDIS - ADVERT




AD

seven
TOUR OPERATOR

@seventouroperator



# ብር ኀደለ ብሎ
# ክጉዝ
# መቅረት ቀረ

ኀደለብኝ ካሉ እኛ **ከዳሽን ባንክ**
ብድር አመቻችተን ፥ ካሰቡት
ተዝናንተው ፣ ኀብኝተው ያለሙትን
አሳክተው ይመለሳሉ።

BW | Best Western. Hotels & Resorts
ዳሽን ባንክ Dashen Bank
seven TOUR OPERATOR

+251961609397
info@seventouroperator.com

እዚህ ጋር ይጫኑ

በአማኑኤል ክንደያ

# ገንዘብ ሳይዝ በሙድ ብቻ

የተወለደው በትግራይ አድዋ አውራጃ እርባ ገረድ በምትባል ትንሽ ቀበሌ ውሰጥ ነው።

የአንድ አጭር ልበወለድና የሶስት መካከለኛ ልቦለዶች ስራ ደራሲ ነው። አምስት ስድስት ሰባት ፣ ትኩሳት ፣ ሰባተኛ መልአክ ፣ ሌቱም አይነጋልኝ በሚባሉ ድርሰቶች ይታወቃል።

በአባቱም በእናቱም ወገን ክህነቱ ይጫነዋል።
አቦይ ገብረእግዚአብሔር ገብረዮሐንስ እና አደይ መዓዛ ተወልደመድህን ከወለደቻቸው 11 ልጆች መካከል ሰብሐት ሰባተኛው ነው።

ሙሉ መጠርያው ስብሐት ለአብ ገብረእግዚአብሔር ይባላል ።
ስብሐት ዛሬም በወጣት አንባብያን ዘንድ በሕሊና እንደተቀመጠ ነው። በስተርጅና ዘመኑ እንኳ ከስነፅሁፍ ስራ አልተለየም። ለ30 አመታት በጋዜጠኝነት ስራ ሰርቷል።



በንጉሱ ዘመን ከሚታተመው አዲስ ዘመን እና ኢትዮጵያን ሔራልድ ጋዜጣ አንስቶ እስከዚሁ ዘመን የነበሩት ስመጥር ጋዜጦች ላይ ፅፏል።

መነን መፅሔት፣ አዲስ ሪፓርተር ከዝያ ወዲህ ደግሞ የካቲት መፅሔት ለዛ የተባሉ መፅሔቶች
አዘጋጅ በመሆን ለአመታት የሰራ ድንቅ ጋዜጠኛ ነው።

በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እግረመንገድ የተሰኘ አምድ በማዘጋጀት ለተከታታይ አመታት ፅፏል።

ቀጥሎም በምእራፍ ጋዜጣ እንደወረደ በሚል አምድ በማዘጋጀት የሰራ ሲሆን በመቀጠልም በአዲስ አድማስ ጋዜጣ በፃፋቸው ፅሁፎች በርካታ ወጣት አንባብያን ማፍራት የቻለና በአገሪቱ ከታዮ የሕትመት መገናኛ ብዙሐን ትልቁ ጋዜጠኛ እሱ ነው ሰብሐት ለአብ ገብረእግዚአብሔር።

በኩራዝ መፅሐፍት መደብር ከአስር አመታት በላይ ሲያገለግል በዝያ ድርጅት ከታተሙት የሚደነቁ መፅሐፍት አብዝሐኞቹ የሰብሐት አሻራ ያረፈባቸው መሆናቸውን በወቅቱ አብረውት የሰሩ ጓደኞቹ ይመሰክራሉ ። አርትኦት ስራ ደግሞ ጥርሱ የነቀለበት ዘርፍ ነው።




ጋዜጠኛ እና አርታኢ ብቻም አይደለም መምህርም ነበር እንጂ።

በአስፋወሰን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ መምህር በመሆን ለሁለት አመት አገልግሏል።

ከአዲስአበባ ዩኒቨርስቲ በኢዱኬሽን የባችለር ዲግሪ ምሩቅ ሲሆን ስብሐት ለአብ የሞያ መነሻ ያደረገው ደግሞ መምህርነት ነበር።

ስብሐት ለ30 አመታት ግድም ሳይታተሙ የቆዩት የሰነፅሁፍ ስራዎቹ የፃፋቸው በተከታታይ ሶስት አመታት ውስጥ ነው። 1958 ትኩሳት ፣ 1959 ሌቱም አይነጋልልኝጠ እንዲሁም 1960 ሰባተኛው መልአክ
ናቸው። እነዚህ መፃሕፍቶቹ የአንድ ሰሞን የገሃዳዊ አለም ጓደኞቹ የተሳተፉባቸው የስነ-ልቦናው ነፀብራቅ ናቸው።

ስብሐት መፅሐፎቹ ከመፃፉ በፊት የአለማችን እውቅ የስነፅሁፍ ሰዎች መፅሐፍት አንብቧል ።
ኢሚል ዞላ ሄሚንግዌይ፣ አንቷን ቼሆቭ የመሳሰሉት ድንቅ ደራስያን ስራ አንብቧል።
ፍልስፍና ስነ-መለኮት፣ ታሪክ ቋንቋ እንዲሁ በጥልቅ ተመስጦ አሰላስሏል ።

ከምእራቡ አለም የፈረንሳይ፣ ከመካከለኛው ምስራቅ ደግሞ የኢራን ስነፅሁፍ ተመሳጭ ነበር።ከድሆች ወገን ሆነህ የምታየውን እንዳለ ፃፈው የሚል ፈሊጥ አለው። የአስተሳሰባችንና የሰነልቦናችን ምሰሶ ነውና ምንም ሳትቀናንስ ፃፈው የሚል መርህ አለው ።

ሁሉን ለገንዘብ ብዬ ሳይሆን ለስሜቴ ስል ፃፍኳቸው ይላል ይህ ታላቅ ደራሲ ። ሰብሐት ገብረእግዚአብሔር በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ ታሪክ ውስጥ ቀድመው ከሚነሱ ዘመናዊ የስነፅሁፍ አስተሳሰብ ካንፀባረቁ መካከል ግንባር ቀደሙ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ሰነ ሰብእ (Naturism) የተሰኘ የሰነ ፅሁፍ ዘውግ በማስተዋወቅ ረገድ ብቸኛው ነው።

በዚሁ የሰነፅሁፍ ዘውግ የሚታወቁት የፈረንሳይ ደራስያን ቢሆኑም ከአገርቤት ዘውግ ጋር በማላመድ ረገድ በብርቱ የደከመ ሰው ነበር።

ዛሬ ሰብሐትን ለማስታወስ የተገደድነው ሚያዝያ 27 ቀን የተወለደባት እለት በመሆኑ ነው።

ጆርጅ ኦልዮት እንደሚለው ከሆነም የሞቱትን የሚያስታውሳቸው ትውልድ እስካለ ድረስ ህያዋን ናቸው ይላል።

ስብሐት ለአብ ገብረእግዚአብሔር ለሚወዳት አገሩ ያበረከተውን ያህል ያልተዘመረለት ትልቁ የሰነፅሁፍ ሰው መሆኑን ማንም ይመሰክራል።

ሰው ምን ለማንበብ ይወዳል ብዬ አልጽፍም።

ሰው የሚወደውን እየመረጠ የሚያቀርብ ነጋዴ ነው ይላል ይኽ ታላቁ የሰነፅሁፍ ሰው።ድርሰት ንግድ አይደለም ይላል እንጂ። ለዛውም እኔ ደግሞ ነጋዴ አይደለሁም። ስነጽሑፍም ጥበብ ነው። የምጽፈው የኮረኮረኝን፣ የተሰማኝ፣ የነካኝን ነው። በዚህ መንገድ ብዙ ላይክ፣ ብዙ ተከታይ አላስከትል ይሆናል።

ይሁን ግድ የለም። ብዙዎች ቢያነቡኝ ደስተኛ የምሆን ቢሆንም፣ ብዙዎች እንዲያነቡኝ ብዬ አንባቢዎቼን አልከተልም ይላል ስብሐት።


እኔ ደራሲ አይደለሁም። ደራሲ የመሆን ህልም ግን አለኝ። ህልሜ ከሰመረ፣ ምኞቴ ከተሳካ አንባቢ እግር ስር እየተከተልኩ የሚንቶሰቶስ የጥበብ ነጋዴ መሆን አልፈልግም ይል ነበር።

ወይም ከብቶችን የሚነዳ እረኛ አልሆንም። ምኞቴ የታየኝን ሚጢጢ ብርሃን ለሌሎች ማሳየት ነው! ህልሜ ሃሳቤን፣ ስሜቴን በጥበብ ሁሉ ለብዙዎች ማካፈል ነው። ብዙ መንጋ ከማንጋጋት ጥቂት ነፍስ ያላቸው አንባቢዎች ጋር መገናኘት እመርጣለሁ የሚለው ስብሐት በኢትዮጵያ ስነፅሁፍና የጋዜጠኝነት ምህዳር ሕያው ሆኖ ይኖራል።

እኛም በዚሁ እትማችን ታላቁ ሰብሐት ለአብ ገብረእግዚአብሔርን ልናስታውሰው ወደናል !

“ሰው ሁሉ እኔን አይቶ ስብሐት ይላል፣
ማን እንደኔ ገንዘብ ሳይዝ በሙድ ብቻ ልጅ ይጠብሳል።”







# ከሰሞኑ ግሎባል ባንክ ያወጣቸው የተለያዩ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ፤ ጨረታው ግንቦት 06/2017 ከቀኑ 8:00 ድረስ ይቆያል

## መኪኖቹን በመጫን ይጫረቱ :መልካም እድል!!


Walia Tender
ዋልያ ቴንደር

## ከመላው ኢትዮጵያ የሚወጡ ሁለንም አይነት የጨረታ ማስታወቂያዎች በቀላሉ!

- ከ **7 አመት በላይ ያለምንም ማቆራረጥ** በታማኝነት፣
- ጨረታዎች በወጡበት ፍጥነት፣
- ተመጣጣኝ ዋጋ ና ለአጠቃቀም ምቹ፣
- በቴሌግራም ፣ በአፕ ና በድረገጽ አማራጮች፣

አሁኑኑ ይመዝገቡ!

+251942125616
+251919415260




www.waliatender.com





መቄዶንያ 8161
ከየካቲት ፩ ቀን ጀምሮ
ታላቅ የገቢ ማሰባሰብያ የቀጥታ ስርጭት
Seifu ON ebs YOUTUBE
Cash App & Zelle
ACC 240-938-2992
gofundme
MEKEDONIA-HELP US BUILD HOME FOR THE HOMELESS
8161
Bank of Abyssinia
coop




እንደ
ጊዜው
ማሚላ ሉቃስ




**የማሚላ ሊቃስ "እንዶ ጊዜው '' አልበም**

ምስሉን በመጫን መዚቃውን ማድመጥ ይችላሉ




**የማሚላ ሊቃስ “እንዶ ጊዜው ‘’ አልበም**

## ምስሉን በመጫን ሙዚቃውን ማድመጥ ይችላሉ




## የማሚላ ሊቃስ “እንዱ ጊዜው ‘’ አልበም

## ምስሉን በመጫን ሙዚቃውን ማድመጥ ይችላሉ


Bored
Cellphone
Addis Ababa


9262
Radio
የሙዚቃና የሬድዮ ዝግጅት
ያለምንም ኢንተርኔት
ቡሁሉም ዓይነት ስልክ
ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም
HOPE
ENTERTAINMENT
taem
ጣዕም


በሁሉም የማህበራዊ ሚዲያዎች
በድምጽ እና በቪዲዮ አማራጭ
አስተማሪ እና አዝናኝ ታሪኮች
እንዲሁም 24/7 በጥራት የሚደመጥ
በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዲጂታል ሬድዮ
Taem Radio
የሚጣፍጥ ታሪክ
ያ ስ ሙ
www.taem.et


ፀሐይ
አትጠልቅም
www.yederaw.com